## ከመቅደስ ሰሎሞን የተወረሰ የሰቀላ ቤተክርስቲያን ሥዕላዊ መግለጫ




የሥዕል 1 መብራሪያ

1. የታቦቱ ሕጉ መንበረ ክብር ያለበት እንዲሁም ቅዱስ ፓትሪያሪኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የሚያስቀድሱበት ሲሆን በዕለቱ የተሰየሙ ሉዕካን ካሕናት መንበሩን ከበው አገልግሎታቸውን ያከናውኑበታል::

2. ድርገት የሚወርድበት / ቀዳሲያን ሥጋው ደሙን የሚያቀርቡበት /

ሀ. ቀራቢዎች በየማዕረጋቸው ሥጋወደሙ የሚቀበሉበት

ሰ. በዕለቱ ተክሊል የተደረገላቸው ሙሽሮች ቆመው አስቀድሰው የሚቆሩብበት

ሐ. መምህራነወንጌል ቆመው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩበት

2.1 በዕለቱ ያልተሰየሙ ቆሞሳት፣ ቀሳውስት ዲያቆናት ቆመው ያስቀዱስበታል።

2.2 ደናግል መነኮሳት ቆመው ያስቀዱሰበታል።

2.3 ለሥጋው ወደሙ ለደጀ ሰላሙ የበቁ አረጋዊናን በዕለቱ ባይቆርቡም ቆመው ያስቀዱሱበታል።

2.4 በዕለቱ ሥጋው ደሙ የሚቀበሉ ወንዶች ምዕመናን ቆመው ያስቀድሱበታል።

2.5 ደናግል መነኮሳይያት ቆመው ያስቀድሱበታል።

2.6 የቀሳውስትና የዲያቆናት ሚስቶች ቆመው ያስቀድሱበታል።

2.7 ለሥጋወደሙ ለደጀሰላሙ የበቁ እናቶች ቆመው ያስቀድሱበታል።

2.8 በዕለቱ ሥጋወደሙ የሚቀበሉ እናቶችና እኅቶች ቆመው ያስቀድሱበታል።

3. ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ስብሐተ እግዚአብሔር ያደርሱበታል፤ ቆመው ያስቀድሱበታል።
ንፍቀ ዲያቆናትና አናጉንስጢሳውያን ቆመው ያስቀድሱበታል

4. ቀሳውስትና ዲያቆናት የመዓልናት የሌሊት ሰዓታት፣ኪዳንና ጸሎተ ፍትሐት ይደርሱበታል።

4 እና 7 የወንዶች መቆሚያና ማስቀደሻ

5 እና 6 የሴቶች መቆሚያና ማስቀደሻ

9የካህናት ብቻ መግቢያ

8.12 የወንዶች ብቻ መግቢያ

11 የጋራ መግልረያ በር

10 እና 13 የሴቶች ብቻ መግቢያ በር

<u>የአቅጣጫ መግለጫ</u>

መስዕ፡ ሰሜናዊ ምሥራቅ ወይም ምሥራቃዊ ሰሜን

ሊብ፡ ደቡባዊ ምሥራቅ ወይም ምሥራቃዊ ደቡብ

አዜብ፡ ምዕራባዊ ደቡብ ወይም በደቡባዊ ምዕራብ

ባሕር፡ ሰሜናዊ ምዕራብ ወይም ምዕራባዊ ደቡብ

# የክብ ቤተ ክርስቲያን ንድፍ ስዕላዊ መግለጫ




ስዕል 2

1. ቅድስት የታቦተ ሕጉ መንበር ክብር ያለበት

ሀ. የክህነት ማዕረግ ያላቸው ካህናት ብቻ የሚገቡበት

ለ. ከቅዱስ ፖትርያርኩ እና ብፁአን አባቶች ሊቀ ጳጳሳት ቆመው ያስቀድሱበታል።

ሐ. ልቡካን /ቀዳሲያን/ መንበረ ክብሩን ዙሪያውን ከበው ጸሎተ ቁርባን ያደርሱበታል/ ይቀድሱበታል።/

## የስዕል 2 መግለጫ

| በታ | አቅጣጫ | ቋሚዎች | የአገልግሎት ዘርፍ |
|---|---|---|---|
| 2. ቅድስት | ምዕራብ | ቆሞሳት<br>ቀሳውስት<br>ዲያቆናት<br>ልቡካን ቀዳሲያን<br>መምህራን ወንጌል<br>ለሙሽሮች | ቆመው ያስቀድሱበታል<br>ይጸልዩበታል<br>ሥጋወደሙ ያቀብሉብታል<br>የእግዚአብሔርን ቃል<br>ያስሙበታል<br>ሥርዓተ ተክሊል ይፈጸምበታል |
| 3. ቅድስት | ሰሜን | ደናግል መነኮሳት<br>የሚቆርቡ ወንዶች<br>ምዕመናን | ቆመው ያስቀድሱበታል፣<br>ይቆርቡበታል፣ ይጸልዩበታል፣<br>ይሰግዱበታል<br>ቆመው አስቀድሰው ይቆርቡበታል |
| 4. ቅድስት | ደቡብ | ደናግል መነኮሳይያት<br>የቀሳውስትና የዲያቆናት<br>ሚስቶች<br>የሚቆርቡ ሴቶች | ቆመው ያስቀድሱበታል፣<br>ይቆርቡበታል፣ ይጸልዩበታል፣<br>ይሰግዱበታል።<br>ቆመው አስቀድሰው ይቆርቡበታል |
| 5. ቅኔ ማሕሌት | ምዕራብ | ለቃውንተ ቤተክርስቲያን<br>መዘምራን<br>ንፍቀ ዲያቆን<br>አናጉንስጢሳውያን | ስብሐተ እግዚአብሔር<br>ያደርሱበታል<br>ዳዊት ይደግሙበታል<br>ቆመው ያስቀድሱበታል<br>ቆመው ለተልዕኮ የሚሰለፉበት |
| 6. ቅኔ ማሕሌት | ሰሜን<br>ምሥራቅ | ቀሳውስትና ዲያቆናት<br>ንዑሳን ክርስቲያን<br>በንስሐ ውስጥ ያሉ<br>ምዕመናን | የመዓልትና የሌሊት ሰዓታት፣<br>የጠዋት ኪዳን፣ ጸሎተ ፍትሐት<br>ያደርሱበታል፣<br>ጸሎ እስኪባል ቆመው<br>ያስቀድሱበታል በጥንተ<br>ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ጥምቀት<br>ያከናውኑበት ነበር<br>ቆመው ያስቀድሱበታል፣<br>ይጸልዩበታል፣ ይሰግዱበታል |